## የዐቃብያነ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ተግባር እና ኃላፊነት

የዐቃብያነ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ጽሕፈት ቤት በአብክመ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 263/2011 አንቀፅ 13(2) የተደራጀ እና በተሻሻለው የክልሉ የአስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 280/2014 አንቀጽ 42 ፊደል ተራ “መ” መሠረት የቢሮው አካል የሆነ ጽ/ቤት ነው፡፡ ጽሕፈት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 263/2011 ዓ.ም ከተደራጀ ጀምሮ በርካታ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

ጽሕፈት ቤቱ ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች መካከልም ዋና ዋናዎቹ:-

- ❖ በቢሮው ተፈጻሚ የሚሆኑና ጽ/ቤቱን የሚመለከቱ ዝርዝር የአሰራር መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፤
- ❖ የዐቃብያነ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ይመራል፣ ይደግፋል፤ ለጉባኤው አባላት ጥሪ ያስተላልፋል፤
- ❖ ለዐቃብያነ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባዔ የሴክሬታሪያት አገልግሎት ይሰጣል፤ በጉባኤው ወይይት ጊዜ ተገኝቶ ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፣ ከጉባኤ በኋላም የጉባኤውን ውሳኔዎች ለቢሮ ኃላፊ ወይም ለጉባኤው ሰብሳቢ ያቀርባል፤ ውሳኔዎች መፈጸማቸውን ይከታተላል፤
- ❖ የዐቃብያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ አባላት እንዲሟሉ፣ አገልግሎታቸውን የጨረሱ አባላት በአዲስ እንዲተኩ እና በአጠቃላይ የጉባኤውን አደረጃጀትና አሰራር የሚያጠናክሩ አሰራሮችን አስመልክቶ ቢሮ ኃላፊውን ያማክራል፣ ያግዛል፤
- ❖ ከዞን ዐቃብያነ ህግ አስተዳደር ንዑስ ጉባኤ ጽ/ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ከዋናው ጉባኤ ጀምሮ በንዑሳን ጉባኤዎች የሚሰጡ ውሳኔዎችን ተግባራዊነት ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ያስፈጽማል፣ የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፤
- ❖ ከንዑስ ወረዳ እስከ ክልል ባሉ በቢሮው መዋቅሮች ውስጥ ያለውን የዐቃብያነ ሕግ የሰው ሃይል እጥረት በመፈተሸ መረጃ ይይዛል፤ ከበላይ አመራሩ ጋር በመነጋገር ሲፈቀድ የደረጃ እድገት ማስታወቂያ እንዲወጣ ያደርጋል፣ ተወዳዳሪዎችን ይመዘግባል፣ ፈተና እንዲወጣ ጥሪ ያስተላልፋል፣ ብቁ የሆኑትን ዐቃብያነ ሕግ ለዐቃብያነ ህግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ አቅርቦ ያሾማል፤

- ❖ ዐቃብያነ ሕግ የሚቀርቡላቸውን ጉዳዮች ገለልተኛ ሆነው በህግና በማስረጃ ብቻ ተደግፈው ውሳኔ እንዲሰጡ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤ ከህግና ከማስረጃ ውጭ በተጽዕኖ ውሳኔ እንዲሰጥ በሚያደርጉ አካላት ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
- ❖ በሚታዩ የአፈፃፀም ክፍተቶች ላይ ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር በመሆን ስልጠናዎችን ያዘጋጃል ውጤቱን ይከታተላል፤
- ❖ ቢሮውን የሚወክል የተደራጀ፣ በቴክኖሎጅ የታገዘ የሰው ሃብት መረጃ እንዲደራጅ ያደርጋል፤
- ❖ በተለያዩ ደረጃዎች በዐቃብያነ ህግ መብቶች ዙሪያ በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ በሚቀርቡ አቤቱታዎች ወይም ቅሬታዎች ላይ ጉዳዩን በመመርመር፤ ለበላይ አመራሩ አስተያየት ይሰጣል፤
- ❖ የጉባኤውን ወይም የኃላፊውን ውሣኔ የማይጠይቁ ጉዳዩች ላይ ምላሽ ይሠጣል፤
- ❖ የክልሉን ዐቃብያነ-ሕግ የግል ማኅደር ያደራጃል፣ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ዉጤቶችና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች በማኅደሮች መግባታቸዉን ይከታተላል፣ የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች የሥራ አፈጻጸም ምዘና ያካሂዳል፤

የክልሉ ዐቃብያነ ህግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ጽ/ቤት በህግ የተሰጡትን ተግባራት እና ኃላፊነቶች ዉጤታማ በሆነ መንገድ በመፈጸም ለቢሮዉ ተቋማዊ ተልዕኮ መሳካት የበኩልን ድርሻ መወጣት ይችል ዘንድ በስሩ የህግ ኦዲት፣ የሥነ ምግባር እና የዲስፕሊን ጉዳዮች መከታተያ ቡድን እና የዐቃብያነ ህግ አስተዳደር ጉዳዮች እና የለዉጥ ስራዎች ቡድን በማደራጀት ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያደረገ የሚገኝ ሲሆን የእነዚህ ቡድኖች ተግባር እና ኃላፊነትም ከዚህ በታች ተመላክቷል፡፡

## 1. የሕግ ኦዲት እና ኢንስፔክሽን ስራን በተመለከተ

- ❖ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 አንቀጽ 28(5) ለቢሮው በተሰጠው ስልጣንና ተግባራት መሠረት ዐቃብያነ-ሕግ የሚያሳልፏቸው ውሳኔዎች በሕግ መሠረት መሰጠታቸውን ያረጋግጣል፤
- ❖ ዐቃብያነ ህግ በሚያከናውኗቸው ተግባራት፣ ለፍ/ቤት በቀረቡ ክሶች፣ በተለያየ መንገድ በምርመራ መዝገብ ላይ የተሰጡ የማቋረጥ ወይም የመዝጋት ዉሳኔዎች፣ የይግባኝ ቅሬታና መልሶች፣ የሰበር አቤቱታዎችና መልሶች እና የተለያዩ አስተያየቶች ሕጋዊነትና

አግባብነት በታቀደ ወይም ድንገተኛ በሆነ ወይም ጥቆማን ወይም የበላይ አመራር ትዕዛዝን መነሻ በማድረግ በሕግ ኦዲት እና ኢንስፔክሽን ሥራ ያረጋግጣል፣

- ❖ በችሎት የሚደረጉ ክርክሮች በቂ ዝግጅት የተደረገባቸውና ክርክሮቹም ህግን መሰረት ያደረጉ መሆኑን በአካል በሚከናወን የኢንስፔክሽን ሥራ ያረጋግጣል፣
- ❖ በየደረጃው የሚገኙ ዐቃብያነ ህግ በሚሰጡት የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የሚነሳን ቅሬታ ተቀብሎ የሚመለከተውን የስራ ክፍል አስተያየትና አስፈላጊ ከሆኑ ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ ውሳኔ ይሰጣል፤የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤
- ❖ ዐቃብያነ ሕግ በተቋሙ የወጡ መመሪያዎችንና የተዘረጉ አሰራሮችን ጠብቀዉ እየሰሩ መሆኑን ያረጋግጣል፤
- ❖ በሕግ ኦዲት ግኝቶች ላይ ተመስርቶ ግብረ መልስና ማስተካከያ እንዲደረግ ለኦዲት ተደራጊዉ የሥራ ክፍል ይልካል፣ የበላይ አመራሩ እንዲያዉቀዉ ያደርጋል ፣
- ❖ በህግ ኦዲት የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ሌሎች የሥራ ክፍሎች እንዲማሩበት ያደርጋል፡፡ ከሚመለከታቸዉ ክፍሎች ጋር በመተባበር ምርጥ ተሞክሮዎችን በስልጠና የማስፋት እንዲሁም ደካማ አፈጻጸም ያሳዩ ባለሙያዎች አቅም ለመገንባት ከሚመለከተው ጋር ይሰራል፤
- ❖ የወንጀል መዝገቦችና ተጠርጣሪዎች/ተከሳሾች ብዛት፣ ስም ዝርዝራቸው፣ የቆይታ ጊዜያቸውና የቆዩበት ምክንያት እና በአጠቃላይ የቅልጥፍና ደረጃውን እንዲሁም ለተፋጠነ ፍትሕ ዕንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን ያጠናል፣ የማሻሻያ ሐሳብ ያቀርባል፣
- ❖ ከሕግ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ግኝት በመነሳት አግባብነት ያላቸው መሻሻያዎች እንዲደረጉ ለሚመለከታቸው አካላት ግብረ መልስ ይሰጣል፣ የማሻሻያ ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮችን በየደረጃው ላሉ ኃላፊዎች ያቀርባል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣
  - ❖ የሕግ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ግኝቱን ለአሰራር ማሻሻያና ለዐቅም ግንባታ ተግባራት እንዲውሉ ለሚመለከተዉ አካል ያስተላልፋል፣
  - ❖ የተቋሙንና የጽ/ቤቱን ዕቅድ መነሻ በማድረግ የስራ ክፍሉን ተግባራት ያቅዳል፣ አፈፃጸማቸውን ይከታተላል ፤ድጋፍ ይሰጣል፤
  - ❖ ለጽ/ቤቱ የሚያስፈልገውን ሰብአዊ እና ቁሳዊ ግብአት እንዲሟላ ያደርጋል፣
  - ❖ በጽ/ቤቱ ያሉ ባለሙያዎችን የክህሎት ክፍተት ለይቶ አቅማቸው የሚገነባበትን ስልጠናና ትምህርት እንዲያገኙ ያደርጋል፤የስራ ክፍሉን ሰራተኞችን የስራ አፈፃፀም ይመዝናል፤

- ከጽ/ቤቱ ተልእኮ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን እና ምርጥ ተሞክሮዎችን ያደራጃል፣
- ለጽ/ቤቱ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን እና ቅሬታዎችን ተቀብሎ ያስተናግዳል ፣ ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል፤
- የጽ/ቤቱን የስራ ክፍሎች የስራ አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ከቡዱኖች ሪፖርት ይቀበላል ፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፣ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት አዘጋጅቶ በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፣

## 2. የዐቃብያነ ሕግ አስተዳደር ጉዳዮች እና የለውጥ ስራዎችን በተመለከተ:-

- የዐቃብያነ ሕግ ስምሪትና የአሰራር ዉጤታማነት ማሻሻያ ስርአት ይቀርፃል ይተገብራል፣
- ብቃት ያላቸዉ ዐቃቤያነ ሕግ ለመሳብና ያሉትን ለማቆየት የሚያስችል አሰራር በመቅረጽ ለሚመለከተዉ አካል አቅርቦ በማፀደቅ ስራ ላይ እንዲዉል ክትትል ያደርጋል፣
- የዐቃቤያነ ሕግ የስራ የምዘና ሥርዓት ከሚመለከተዉ ጋር በመሆን ይቀርፃል፣ በየወቅቱ እንዲመዘኑ ይከታተላል፣ ዉጤቱን ከማህደራቸው ጋር እናዲያያዝ ያደርጋል፣
- ከጉባኤዉ ጋር በመሆን ለተቋሙ የሚያስፈልጉ ዐቃቤያነ ሕግ የስራ መደብ እና ደረጃወች አይነት፣ብዛትና ተፈላጊ ችሎታ ሰነድ ያዘጋጅል፣ ለሚመለከተዉ አካል አቅርቦ በማፀደቅ ስራ ላይ እንዲዉል ክትትል ያደርጋል፣
- ክፍት የሥራ መደቦችን በመለየት ዐቃቤያነ ሕግ በዝውውር በደረጃ ዕድገት፣ በቅጥር፣ እንዲሟሉ ያደርጋል፣
- የዐቃብያነ-ሕግን ሹመት፣ ምደባ ዝውውር፣ የዕረፍት ጊዜ፣ የአገልግሎት ዘመን፣ ሥነ-ምግባር፣ አደረጃጀት፣ መዋቅር፣ ደረጃ እድገት፣ ደመወዝ፣ መልቀቂያ፣ ጥቅማ ጥቅም እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ አግባብ ባላቸው አካላት የተሰጡ ውሳኔዎችን ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፤
- የጉባኤው ውሳኔ የማይጠይቁ የዐቃቤያን ሕግ የእርስ በእርስ ዝውውና ሌሎች ተመሳሳይ ድጋፎችና ዕለታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፣
- በዐቃብያን ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባዔ ለሚዘጋጁ የተለያዩ መመሪያዎች ለሚሰጡ ውሳኔወች ግብአት የማሰባሰብ ስራ ይሰራል፤ መነሻ የሚሆኑ ረቂቆችን ያዘጋጃል፤
- ለዐቃብያነ ሕግ የስራ የዝውውር የደረጃ እድገትና የቅጥር የማስተዋወቂያ ያወጣል ይመዘግባል መረጃውን አደራጅቶ ለውሳኔ ያቀርባል፤

- ❖ በፈተና ሊለይ የሚገባው የደረጃ ዕድገት ውድድር በሚኖር ጊዜ የፈተና ቀኑ ሲደርስ ሶስት ቀን ሲቀረው ተወዳዳሪወችን ፈትነው ውጤት የሚያስተላልፉ ባለሙያወች በቢሮ ኃላፊው እንዲሰየሙ ያሳውቃል፣ በዚሁ አግባብ የተላለፈለትን ውጤት መዝግቦ ለውሳኔ ያቀርባል፡፡
- ❖ የዐቃቤያን ሕግ ደህንነትና ጤንነት እንዲጠበቅ ለሠራተኞች ተስማሚና ምቹ የሥራ አካባቢ እንዲፈጠር በሥራ አካባቢ የሚኖሩ ችግሮችን በመለየት የመፍትሔ ሀሳብ ማቅረብ፤ ማስወሰንና ተግባራዊ ማድረግ፤
- ❖ በተለያየ ምክንያት ስራ ያቋረጡና ከስራ ገበታቸው የተለዩትን ዐቃብያነ ሕግ ወቅታዊ መረጃ ይሰበስባል እንደየምክንያቱ ለይቶ ለውሳኔ ያቀርባል፣
- ❖ የዐቃብያነ ሕግን የግል ማህደር አደራጅቶ ይይዛል፣ በቴክኖሎጅ የታገዘ የመረጃ ቋት ያደራጃል፣የመረጃ አያያዝ ስርዓቱን ያዘምናል፣ ያስተዳድራል፣
- ❖ ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር በመሆን የአገልግሎት አሰጣጥ እስታንዳርዶች እንዲዘጋጁ ይደግፋል፣
- ❖ በቢሮዉ የሚሠጠዉን አገልግሎት እና የተገልጋዩን የእርካ ደረጃ ለመለየት የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል፣
- ❖ የለውጥ ፕሮግራሞችን ይከታተላል፡፡
- ❖ ከተቋማችን አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የሚነሱ የዉስጥ እና የዉጭ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየት እቅድ ያዘጋጃል፣ተፈጻሚነታቸዉንም ይከታተላል፣ግብረ መልስ ይሰጣል፣

### 3. የዐቃብያነ ሕግ የስነ-ምግባር እና የዲሲፕሊን ክትትልን በተመለከተ፡-

- ❖ በኦዲት ግኝት የደረሰበትን ወይም ከየስራ ክፍሎች የሚላክለትን የዐቃብያነ ሕግ የስነ-ምግባር ግድፈት አስተያየትና ጥቆማ መነሻ በማድረግ ምርመራ ካጣራ በኋላ ለበላይ ኃላፊው የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ በሚሰጠው ትእዛዝና ውሳኔ መሰረት የዲሲፕሊን ክስ ለጉባኤው አቅርቦ ተከራክሮ ያስወስናል ወይም የክስ አይቀርብም ውሣኔ ይሠጣል፤
- ❖ ይግባኝ ለፍርድ ቤት ሲቀርብ መልስ ይሰጣል፣ይከራከራል፤ውጤቱን ለስራ ክፍል ኃላፊውና ለበላይ ኃላፊው ያሳውቃል፡፡

## 4. የዐቃብያነ ሕግን የትምህርት እና ስልጠና በተመለከተ፡-

❖ የተቋሙን የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች ከአገሪቱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ጋር በማጣጣም ይቀርፃል፣ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣

❖ እንደ የስራ ባህሪያቸው የዐቃቢያነ ሕግን የአጭር፣የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ስልጠና እቅድ ያዘጋጃል፣ ይፈፅማል፣ያስፈፅማል፣

❖ የዐቃቢያነ ሕግን የትምህርትና የስልጠና መመሪያና ማኑዋል ይቀርጻል፣ያጸድቃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

❖ የትምህርትና ስልጠና ፍላጎት የዳሰሣ ጥናት በማካሄድ የአጭርና ረጅም ጊዜ የትምህርትና የስልጠና ፕሮግራሞችን ይቀርፃል፣የስልጠና አሰጣጥ መንገዶችን ይወስናል፣

❖ የአጫጭር ስልጠና ፍልጎት ዳሰሳ ያካሄዳል፣የስልጠና ፕሮግራሞች ይቀርፃል፣ ሰልጣኞችና አሰልጠኞች የሚመለመሉበት መስፈርት ያወጣል፣የስልጠና ዘዴዎችን በመለየት ስልጠና ይሰጣል፣

❖ ሰፊና ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆይ ስልጠና ፍላጎት በመለየት ከፍትሕ ባለሙያወች ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት እና በሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፣

❖ ልዩ ክህሎት የሚጠይቁ የስልጠና መስኮችን በመለየት ዐቃቢያን ሕግ የረጅምና የአጭር ጊዜ የቅድመ ስራ ላይ ስልጠና እንዲወስዱ ያደርጋል፡፡

❖ የዐቃብያነ ህግ የሰው ሃብት አቅም ግንባታ ሥራን ለመተግበር በየጊዜው የሚወጡትን መመሪያዎችን ለማስተዋወቅ ሴሚናሮች ወርክሾፖች እና ሲፖዚየሞች ያዘጋጃል ያስተባብራል፣

❖ ከተለያዩ ማስልጠኛና የትምህርት ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ትምህርትና የስልጠና ዕድሎችን ያፈላልጋል፣ በተገኙ የአጫጭርና የረዥም ጊዜያት ስልጠናዎች ዐቃብያነ ህግ ተጠቃሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣በዕጩዎች የሚሞሉ የግዴታ ውል ቅጾችን ያጸድቃል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣